## የመስዋ ሽምብራ

አለወቅት ያሸተች የፍትህ ሽምብራ
በፈጠራ ወንጀል ባሰት ተጠርጥራ
በዘር ተንዘርዝራ በመለስ አምልኮ
ቀጥቅጦ ለመግዛት ሕዝቡን አንበርክኮ
ያለመው ዓላማ ያፈና ፀጥታ
ተመስገን ደስ አለኝ የማታ የማታ
በዓለም አቀፍ ጩኸት ማነቆው ተፈታ።

## የቃዬል ገመና

በቅናት አባዜ ወንድሙን በመግደል
ጌታቸው ማሩና ብርሃነ መስቀል
እንደጠፋው ሰጥሞ በአቤል ደም አረንቋ
ሰልጥነው እነርሱም በመሳሪያ ቋንቋ
"ሀ" ና "ለ" ነበሩ በሞት አማርኛ
ቃዬልን ያስንቁት በወንድም ደመኛ።

## አያመኝም ተውኩት

ክርስቶስ ና ሲለው ፅዋው ሞልቶ ሲፈስ
ጳውሎስን ከኋላው አስከትሎ መለስ
ካዘንተኛ ዕለቅሶ የእምባ ፀበል ቋጥሮ
መጓዙን ስሰማ በሰው ደም ተነክሮ
ሃያ ዓመት በሙሉ ቆስየ የኖርኩት
ያመኝ የነበረው አያመኝም ተውኩት።

ነሃሴ 2004 ዓ.ም
አብርሃም በየነ